

መልክአ እግዚአብሔር አብ

ፀጋን የምታድል የመከራና የችግር ጊዜያትንም የምታሰግድ ፍፁም ዘለዓለማዊ አምላክ *እግዚአብሔር አብ ሆይ* ልመናውን የማታቋርጥ ነፍሴ አስቀድሞ ነብያትህ ሄኖክንና ዕዝራን ማስተዋልን እንደመላኋቸው ንጉሰን ከወታደሮች ጋራ የሚያጸና ይቅርታህ ይርዳኝ ትልሃለች ። አሜን

ወዳጅህ እስራኤልን አፍህን ክፈት እኔም አመለዋለሁ ያልኸው *እግዚአብሄር አብ ሆይ* አንተ ርኅርኅና ፍፁም አምላክ ነህ ምስጋናህን አቀርብ ዘንድ አንደበቱን አዘጋጃለሁ።

በደሴተ ፍጥሞ ለነበረ ቅዱስ ዮሐንስ ራእይን የገለፅህ *እግዚአብሔር አብ ሆይ* ጉድለት ችልታ በሌለበት በአዲስ አንደበት የመፅሐፍት ምሥጥራትን አንብቤና ተርጉሜ ህግህን ለማስተማር የጀመርሁትን አዲስ ግብር እፈፅም ዘንድ አቤቱ ፀጋህን አድለኝ ። አሜን

ከዘመናት አስቀድሞ የነበርኽ የዘመናት ባለቤት ዘመናትንም አሳልፍኽ የምትኖር በባሕርይህ ጉድለት የሌለብህ በፍጡራን ሁሉ አንደበት የምትመሰገን *እግዚአብሔር አብ ሆይ* ዘመናትን በፀጥታ የምታፈራርቅ አንተ ነኽና ፈጽሞ *ለተመሰገነ ዝክረ ስምህ ሰላምታ ይገባል* ።አሜን

ከእግዚአብሔር ወልድ እና ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ጋርራ ዕሩይ የሆንኽ የብርሃኑ ክበብ ለሚያስደንቅ የራስ ፀጉርህና ምሳሌ የሌለው ምስጋና የሚገባህ *እግዚአብሔር አብ*ሆይ የሦስትነት የአንድነታችህ ፀሐይ ለዓለም ሁሉ ጌጥ ኾኖ ከምዕራብ እስከ ምሥራቅ ከምድር እስከ ሰማይ ያበራል የኹላችን መለያ ክብርህ ሰማያትን የመላ ጌትነትህም ፈጽሞ የተመሰገነ *እግዚአብሔር አብ ሆይ*ከኹለቱ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ጋራ ብርሃን በማስገኘቱ ፈፅሞ ለተመሰገነ ገፅህ ሰላምታ ይገባል ። አሜን

የብርሃናት ፈጣሪ ሆይ ጨለማ ለማይስማማቸው ብሩሃት አይኖችህና ቅንድቦችህ ሰላምታ ይገባል። አሜን ኃይልና ምስጋናም ለአንተ ይገባልና አይኖቼ በሞተ

ኃጢአት እንዳያንቀላፉ በብርሃን እረድኤትህ ንቁሓን አድርጋቸው።አሜን

የምስጋና ምስዋዕት የምትቀበል *አግዚአብሔር አብ ሆይ* ሁልጊዜ ፀሎትን ለሚያዳምጡና የሚያንፀባርቅ እሳትን ለተጎናፀፉ ጉንጮችህ ሰላምታ ይገባል ።አሜን አቤቱ ዘወትር እንደ አሸኮኮ የምጨነቅበት የጭንቅ ጩኸቴን ታሰወግድልኝ ዘንድ ኤሎሄ ኤሎሄ እያልሁኝ የምለምንህ ፀሎቴን ተቀበልኝ። አሜን

በኹሉም ሁሉ ሥፍራ የነበርህና ያለህ የምትኖር ሳንታው በተባሉ ስሞችሁ የምትመሰገን በባሕርይህ ህልፈት ሽረት የሌለብህ *እግዚአብሔር አብ ሆይ* የሚያስደስት መዓዛን ለተመሉ አፈንጫዎችህና ዳግመኛም የተወደደ ቃል በሚሰማባቸው ከንፈሮችህ ሰላምታ ይገባል። አሜን

ዓለም ሳይፈጠር አስቀድሞ የነበርህ አዲሱ ዓለም ከተገለጠ በኋላ ለዘላለም የምትኖር ጌታዬ ነህ በፍፁም ምስጋና የተመላህ ዘላለማዊ አምላክ *እግዚአብሔር አብ

ሆይ* በተወደደ አንደበትህና መለኮታውያን ለኾኑ ጥርሶችህ ሰላምታ ይገባል ። አሜን

በእጅ መሃል ዓለምን የያዝህ *እግዚአብሔር አብ ሆይ* ወዶ ፈቅዶ ለሚናገር አንደበትህና እንደ ነጎድጓድ ለሚያስተጋባ ድምፀ ቃልህ ሰላምታ ይገባል ። አሜን በአንተ ዘንድ ህልው የኾነ ኹሉን የሚገልጥ መንፈስ ቅዱስ የእየነገዱን ቋንቋ ኹሉ ይግለጥልኝ። አሜን

ፅድቅንና ይዋሄን.የትህትናንም ግብር ሁሉ የምትወድ ጠላት ሳጥናኤልን የጣለውን ትዕቢትን የምትጠላ ገናንነትህ እጅግ የሚያስደንቅ *እግዚአብሔር አብ ሆይ* የሕይወትና የጤና እስትንፋስ በኾነ እስትንፋስህ የፀጥታ ደጃፍ የሃይልም መገለጫ ለሆነ ጉሮሮህ ሰላምታ ይገባል። አሜን

እግዚአብሔር አብ ሆይ

ርዝመቱ በሚያስደንቅ ዙሪያውም ክብ ለሆነ መጠኑ ለማይታወቅ ጽሕምህ ሰላምታ ይገባል። አሜን በዝናም እረድኤትህ ጠልና ከፍታው እጅግ በበዛ የይቅርታህ ደመና የሕይወቴን ጽድቅ እንደ ካህኑ አሮን ፂም አርዝምልኝ። አሜን

ከመገለጥ ይልቅ የተሰወረውን የበልጥ የምትሰውር *እግዚአብሔር አብ ሆይ* ዕበየ ግርማህ ለከበበው አንገትህና ዳግመኛም በአንድነት ለጸኑ ትከሻዎችህ ሰላምታ ይገባል። አሜን የባህርይ ልጅህ ኢየሱስ ክርስቶስ እንክርዳዱን ከስንዴው ለይቶ በእሳት ሲያቃጥል ብጽላሎተ ረድኤቱ ይሰወውረኝ። አሜን

ጥልቅ ባህር ጥበባት *እግዚአብሔር አብ ሆይ* ኪሩብ ሊሸከመው ለማይችለው ጀርባህና ዳግመኛም አርባብ የተሰኙ የዋሃን ነገደ መላእክት ላይ ከብሮ ገንኖ ለሚኖረ ቅዱስ ደረትህ ሰለምታ ይገባል። አሜን ኪነ ጥበቡ እጅግ የሚያስደንቅ ኃይልህ እኔ ጠቢብ ልጅህን ከስንፍና ይልቅ ጥበብን ያድለኝ። አሜን

የክብርህን ነገር ለመናገር የሚያስደንቅ በማስተዋል ለሚሰሙት እጅግ የከበደ ለመንግስትህም ፍፃሜ የሌለህ *አግዚአብሔር አብ ሆይ* የፀጋ ብርሃናትን ለሚያፈልቅ ሕፅንህና ዳግመኛም ዓለምን ለመመገብ ለተዘረጉ የምህረት እጆችህ ሰላምታ ይገባል። አሜን

ደዌን የምትፈውስ *እግዚአብሔር አብ ሆይ* ለአሸናፊ ድል ለሚያነናፅፉ ክንዶችህ እና አካልህ ጋር ለተስማሙ ክርኖችህ ሰላምታ ይገባል። አሜን የሐጥያቴን ደዌ አውሬ ዲያብለስን በወጋህበት ጦር ወግተህ በአዳኝ ኃይልህ ኢድነን ። አሜን

ከእግዚአብሔር ወልድና ከእግዚአብሔር መንፍ ቅዱስ ጋራ በእሳታዊ ዙፋንህ ከብረህ ገንነህ የምትኖር ዓለም ሳይፈጠር አስቀድም ሥልጣነ የባህርይህ የሆነ *እግዚአብሔር አብ ሆይ* ለሚያስፈራ አምላካዊ ክንድህና ይህን ስፊ ዓለም ለያዘ መሐል እጅህ ሰላምታ ይገባል። አሜን

የፍቅርና የቸርነት መገኛ በሰማያትና በምድር በየብስና በባህር ያሉትን ፍጥረታትን ኹሉ የምትመግብ *እግዚአብሔር አብ ሆይ* ይህን ዓለም ለፈጠሩ ጣቶችህና ድንቅ ሥራዎችህን ለሚያፈጥኑ ጥፍሮችህ ሰላምታ ይገባል። አሜን



ከንፎቻቸው ስድስት የኾኑ ኪሩቤልና ሱራፌል አንተን ዘወትር ከባህርይ ልጅህ እግዚአብሔር ወልድና ከባህርይ ሕይወትህ ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ጋራ የሚያመሰግኑህ *እግዚአብሔር አብ ሆይ* ልብሱ መብረቀ ስብሐት ለኾነ ጎንህና የመኖሪያ ሥፍራ *ለማይወሰነው ሆድህ ሰላምታ ይገባል*።

ይቅርታህና ርኅራኄህ ብዙ ነውና በፍጡራን አንደበት ኹሉ የምትመሰገን እግዚአብሔር አብ ሆይ ቅንና የዋህ ልብህና የዘመናትን ፍፃሜ አስቀድሞ ለሚያውቅ ሕሊናህ ሰላምታ ይገባል ክንድህም ለይቅርታ ዘወትር የተዘረጋ ነው ።

።በለይም በታችም ለዘመለአለም ነግሠህ የነበርህና ያለህ የምትኖር ንጉሥ ነገሥት እግዚአብሔር አብ ሆይ መልኩ ለሚያስደንቅ ጎንብርትህና ዳግመኛም *ለትጥቁ ደግ ለሚያምር ሐቄህ ሰላምታ ይገባል* አቤቱ ኃይልህ አሸናፊ ነውና የዐመፃ አውሬ ዳቢሎስን አሸንፍ ዘንድ የትዕግስትን ትጥቅን አልብሰኝ። አሜን

የእግዚአብሔር ወልድ የባህርይ አባት እግዚአብሔር አብ ሆይ ክቡድና መለኮታዊ ለኾኑ ጭኖችህ ዳግመኛም *ለጉልበቶችህ ሰላምታ ይገባል*። አሜን ጠላት ዳቢሎስ ከሰጠኸው ሰልጣኑ ከተባረረ ቡኃላ ትጉሀን ሰማይ የሆኑ ነገደ መላእክት በአንድነት አመሰገኑህ

ዓለም ሳይፈጠር አስቀድሞ የነበርህ ምድርንም የዘረጋህ ሥራህንም በድንቅ በማስተዋል ከመሥራትህ አስቀድሞ የምትኖር እግዚአብሔር አብ ሆይ ምድርን ለሚያንቀጠቅጡ እግሮችህና ከእግርህ *መረገጫም ጋራ ለተረከዝህ ሰላምት ይገባል*። አሜን

የአባታችን አዳም የህይወቱ መሰረት *እግዚአብሔር አብ ሆይ* ከአካልህ ጋራ ሳይለዩ ለሚኖሩ አስሩ ጥፍሮችህና ጣቶችህም ሰላምታ ይገባል። አሜን

ልቤ ለመዳን ይሻልና ለዘለአለማዊነትህ ከከንቱ ሞት ጎጢአት ያድነኝ ዘንድ እማፀንህ አለው ። አሜን

ለመንግሥትህ ፍፃሜ የሌለው ቃልህና አካልህ

በመልክዕና በቁመት እጅግ የከበረ የምትደነቅ የብርሃናት መገኛ *እግዚአብሔር አብ ሆይ* ከአቅም በላይ በኾነና ለመይወሰን አካለ አቅምህና ዳግመኛም ግርማ ራእዩ ለሚያስደንቅ መልክዕህ ሰላምታ ይገባል ። አሜን

አንተ እውነተኛ አምላክ ሥትሆን ኹሉን በፈቃድህ የፈፀምህ የኹሉ ፈጣሪ *እግዚአብሔር አብ ሆይ* ኹሉን ማድረግ የሚቻልህ ሁሉ ለአንተ የቀረበ በአንተም ዘንድ አለና በእውነተኛይቱ መንገድ መርተህ ህግን አስተምረኝ። አሜን

እግዚአብሔር አብ ሆይ በለሊትና በቀኑ ሙሉ ምስጋና ይገባሃል። አሜን

እግዚአብሔር አብ ሆይ በክረምት እና በበጋ አውራጎ ልክ ምስጋና ይገባል ። አሜን

እግዚአብሔር አብ ሆይ በየቀኑና በየለሊቱ ሁሉ ምስጋና ይገባሃል። አሜን

እግዚአብሔር አብ ሆይ በማይታየውም ኹሉ ዘንድ ምስጋና ይገባል።አሜን አለም ሳይፈጠር አስቀድሞ የነበረና የአለ የሚኖርም ምስጋናህን እነሆ ሰማይ ይናገራል አቤቱ *እግዚአብሔር አብ ሆይ* ከሥጋና ነፍስ መከራ እኔን ጠብቀኝ ብርሃንህንም አብራልኝ ለዘላለሙ አሜን ።*አባታችን ሆይ*